## ፖሊሲ JB-R-2፡- የ1973ቱን መልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ክፍል 504 ("ክፍል 504") እና የክፍል 504 የቅሬታ አሰማም ደንቦች የአተገባበር ሕግ

የሚከተለው ደንብ የወጣው የት/ቤት ቦርድ ፖሊሲ JB - ከአድሎ የፃ እና እኩል የትምህርት ዕድልን ለማስፈጸሚያ ነው። ይህ ሕግ የተቀረፀው በፖሊሲ JB ውስጥ እንዲሁም በፌደራል እና የስቴት ሕጎች እና በአካባቢ መመሪያዎች ውስጥ ከተቀመጡ ጠቅላላ ዓላማዎች እና መርሆች ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ነው።

የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤት በክፍል 504 እንደተገለጸው በዲስትሪክቱ ውስጥ ለሚገኙ የአካል ጉዳተኛ ልጆች በክፍል 504 እና በሥራ ላይ በዋሉት አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተጠየቀው መሠረት የነፃ እና ተገቢውን የሕዝብ ትምህርት (“FAPE”) ይሰጣል። በክፍል 504 በተገለጸው መሠረት FAPE ለሚያስፈልገው ወይም ያስፈልገዋል ተብሎ ለሚታመን ለማንኛውም ተማሪ ዲስትሪክቱ በዚህ ሕግ ውስጥ የተዘረዘሩትን ደንቦችን እና በክፍል 504 ("504 እቅዶች") መሠረት የተቀበላቸውን እቅዶች ይከተላል።

### ትርጓሜዎች

1. "የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት" /“Student Compliance Officer”/ ማለት የክፍል 504 ሕጎች እና ደንቦች መከበራቸውን የሚቆጣጠር የተማሪዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይም የወከሉት ተዋካይ ማለት ነው።
2. "ቅሬታ አቅራቢ ግለሰብ" /“Aggrieved Individual”/ ማለት በክፍል 504 መሠረት አካልጉዳተኞች ተብለው የተለዩ ተማሪዎችን ለFAPE በመለየት እና አገልግሎቶችን በመስጠት ረገድ የቦርድ ፖሊሲዎች ጥሰት ምክንያት በቀጥታ ጉዳት የደረሰበት እና/ወይም ለተባለው ጥሰት ምስክር የሆነ የዲስትሪክቱ ተማሪ ወይም ወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ ማለት ይሆናል።

### የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባራት

የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም በየት/ቤቱ ያለ ተወካዩ/ዋ ክፍል 504 ተከትለው የሚቀርቡ የብቁነት አወሳሰኖች እና ሁሉንም የቅሬታ አቀራረብ ደንቦችንና ሂደቶችን ለማንኛውም FAPEን ብቁ ለሆኑ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በክፍል 504 መሠረት መስጠትን የሚጠይቁ የፌዴራል ወይም ስቴት ሕጎች ወይም የቦርድ ፖሊሲ ጥሰት ጥያቄዎችን የማጥራት እና የማስተባበር ኃላፊነት ይኖርበታል።

የዲስትሪክቱ የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ አድራሻ፡-

ዋና ሥራ አስፈፃሚ<br>
የተማሪዎች አገልግሎት<br>
ዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች<br>
1860 Lincoln St.<br>
Denver, CO 80203<br>
ሥልክ ቁጥር፡- (720) 423-3769

### የተማሪ 504 እቅዶች

ADA እና ክፍል 504 አካል ጉዳተኝነትን እንደሚከተለው ይፈታዋል/ይተነትነዋል፡- (i) አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሕይወት እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ የሆነ ገደብ የሚያደርግ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት፣ (ii) የእንደዚህ ዓይነት ጉዳት ምዝገባ/ማስረጃ፣ ወይም (iii) እንደዚህ ዓይነት ጉዳት ያለው ተደርጎ መቆጠር/መታየት።

በሥራ ላይ በዋሉ ሕጎች መሠረት፣ የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤት በክፍል 504 መሠረት ተቀባይነት ያላቸው የአካል ጉዳቶች ላሉባቸው ተማሪዎች FAPE ይሰጣል። በእቅድ 504 መሠረት አንድ ተማሪ አገልግሎቶች ፈላጊ ነው/ናት ብለው የሚያምኑ

ተማሪዎች እና/ወላጆች የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊን እና/ወይም በት/ቤቱ የወከሉትን ቀጠሮ በመጠየቅ ስለ ተማሪው/ዋ የ504 እቅድ ብቁነት እንዲወያዩ ይበረታታሉ። እንደዚሁም፣ በእቅድ 504 መሠረት አንድ ተማሪ አገልግሎቶች ፈላጊ ነው/ናት ብለው የሚያምኑ ሁሉም የዲስትሪክት ሠራተኞች የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊን ወይም በት/ቤቱ የወከሉትን ተዋካይን ስለ ተማሪው/ዋ የ504 እቅድ ብቁነት ለመወያየት የስብሰባ ቀጠሮ እንዲይዙ በመጠየቅ ይችላሉ።

የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ  ስለተማሪው/ዋ የሚያውቁ፣ የተማሪውን/ዋን ት/ቤት ታሪክ የሚያውቁ፣ የተማሪውን/ዋን የግል ፍላጎቶች የሚያውቁ፣ የማንኛውንም የግምገማ ዳታ ትርጉም የሚረዱ እንዲሁም የአገልግሎቶች አማራጮችን የሚያውቁ ሰዎች ቡድን ("ቡድን 504") ያዋቅራል። የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ በቡድን 504 ውስጥ የተማሪው/ዋ ወላጅ(ጆች) ወይም አሳዳጊ(ዎች) እንዲኖሩበት ጥረት ያደርጋል።

የተማሪዎች ቡድን 504  ለእቅድ 504 ጥያቄ የቀረበውን ማመልከቻ ተመልክተው የተማሪውን/ዋን ለእቅድ 504 ብቁነትን ለመወሰን ግምገማዎች ያስፈልጋል አያስፈልግም የሚለውን የቀረበ ሀሳብ (ሪፈራል) ይመለከታል። ለእቅደ 504 ብቁነትን ለመወሰን ዲስትሪክቱ የግምገማ ውጤት ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም ግን ለእቅደ 504 ብቁነትን ለመወሰን ዲስትሪክቱ የግምገማ ውጤት ከጠቀ ዲስትሪክቱ ግምገማውን በራሱ ወጭ ያስደርጋል።

በክፍል 504 መሠረት የአካል ጉዳተኛ ተብሎ የተለየ ተማሪ ምን አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት የመወሰን ኃላፊነቱ የቡድን 504 ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎችን በሚወስኑ ጊዜ፣ የተማሪው ቡድን 504 የተገኘውን ጠቃሚ መረጃ ሁሉ መመልከት ይኖርበታል፤ እንዲሁም የተማሪው ወላጅ(ጆች)  ወይም አሳዳጊ(ዎች) የተማሪው አገልግሎቶች በሚወሰኑበት የቡድን 504 ስብሰባዎች እንዲገኙ መጋበዘ ይኖርባቸዋል። የተማሪውን ብቁነት ሲወስኑ እና ለተማሪው/ዋ የሚሰጡትን ተገቢ ትምህርታዊ አገልግሎቶች ሲያቅዱ የተማሪው ቡድን 504 የJB-E ቅጽን መሙላት ይገባቸዋል፡- "የክፍል 504 እቅድ"

ተማሪው/ዋ በክፍል 504 መሠረት የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ቢሆንም/ብትሆንም፣ የ504 ቡድን ተማሪው ምንም ዓይነት አገልግሎቶች ተገቢ አይሆኑለትም/ላትም ብሎ ሊወስን ይችላል። በዚያ ሁኔታ፣ ቡድን 504 ተማሪው በክፍል 504 መሠረት የአካል ጉዳተኛ መሆኑን ነገር ግን የትምህርታዊ ከባቢዎችን ለመድረስ የተለዩ አገልግሎቶች ማግኘት የማይገባው እንደሆነ በጽሑፍ ፋይል አድርጎ ያስቀምጣል።

**የተማሪ መሻሻል ክለሳ**

የተሰጡት አገልግሎቶች ተገቢ እና አስፈላጊ መሆናቸውን ለመመገምገም እና የተማሪው/ዋ ፍላጎቶች የአካል ጉዳት እንደሌለባቸው አቻዎቹ/ቿ በበቂ ሁኔታ መሟላቱን ለማረጋገጥ የተማሪው ቡድን 504 የተማሪውን መሻሻል እና የተማሪውን እቅድ 504 ውጤታማነት በየዓመቱ ይገመግማል። የተማሪው/ዋ ወላጅ ወይም አሳዳጊ በክፍል 504 መሠረት ዲስትሪክቱ የአካል ጉዳተኛ ተማሪን የመለየት ሂደትን፣ ግምገማን ወይም ምደባን በተመለከተ የሚወስነውን ማንኛውንም ውሳኔ በጽሑፍ እንዲያውቁት ይደረጋል።

**የቅሬታ አቀራረብ ሂደት**

በክፍል 504 እና ወይም ከዚያ ውጭ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ለሚቀርቡ ክሶች፣ በክፍል 504 መሠረት ተገቢ የትምህርታዊ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸው ወይም ያስፈልጋቸዋል ተብሎ ለሚታመኑ ተማሪዎች የሚደረግ የመለየት ሂደቱን፣ ግምገማውን፣ ትምህርታዊ ምደባውን ወይም የአገልግሎቶች አሰጣጡን የሚቃወሙ የቅሬታ አቅራቢው ግለሰቦች ለዲስትሪክቱ የተማሪዎች ቅሬታ ሰሚ ኃላፊ ማቅረብ ይችላሉ። ቅሬታዎች በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ቅሬታ አቅራቢ ግለሰቦች AC-E-2 ቅጽን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ። “የመድሎ/የጥቃት ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ” መምህራን፣ አማካሪዎች፣ ርዕሰ መምህራን፣ ወይም የዲስትሪክቱ ሠራተኞች የደረሳቸውን ሁሉንም ሪፖርት ወዲያውኑ ለተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ማስገባት አለባቸው።

ሁሉም አቤቱታዎች/ክሶች የክሱን ክስተት እና በክስተቱ የተሳተፉ ሰዎች ስም(ሞች)፣ ምስክሮች ካሉም ምስክሮችን ጨምሮ ዝርዝር መግለጫዎችን ማካተት ይኖርባቸዋል። የቅሬታው መግባት ያለበት ተማሪው እና/ወይም ወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው ያልተስማሙበት የቡድን 504 ውሳኔ በደረሰበት በ30 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት።

የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ጉዳዩን አጣርቶ ለቅሬታ አቅራቢው/ዋ ግለሰብ በዚህ ደንብ መሠረት ስለ አሏቸው መደበኛ እና ኢ-መደበኛ መብቶች እና አማራጮች የሚያሳውቅ ተወካይ ይሰይማል።

በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ደርሰዋል በተባሉ መድሎዎች ላይ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች በJB-R1 ውስጥ የተዘረዘሩት ደንቦች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ልብ ይበሉ።  ያ ሂደት አቅራቢው/ዋ ግለሰብ ከመለየት ሂደቱ፣ ከግምገማው፣ ወይም ከትምህርታዊ ምደባው ጋር በተያያዘ በዚህ ውስጥ የተሰጠውን የቅሬታ አፈታት ሂደትን ተከትሎ መፍትሄ የማግኘት መብቱን/ቷን የሚከለክል አይሆንም።

## ኢ-መደበኛ የግልግል ሂደቶች

የተማሪዎች ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ኢ-መደበኛ ለሆነ የግልግል ሂደት ጥያቄ ከቀረበለት በክፍል 504 ላይ ስልጠና የወሰደ አንድ የዲስትሪክቱ ሠራተኛ የግልግል ሂደቱን እንዲያመቻች ይመድባል።  በኢ-መደበኛ የግልግል ሂደቱ የተገኘው ማንኛውም ስምምነት ለሁለቱም ወገኖች በጽሑፍ ይሰጣል።  ይህ ሂደት ቅሬታ አቅራቢው/ዋ ግለሰብ ሌላ የዲስትሪክት ክፍል 504 ቅሬታ አፈታት ሂደቶችን እና/ወይም በፍታ ብሔር ቢሮ መደበኛ ክስን የማስጀመር መብት አይነካም።

## መደበኛ የችሎት ደንቦች/ሂደቶች

በ1973ቱ የመልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ክፍል 504 መሠረት ጥበቃ ለሚገባቸው ተማሪዎች ለሚሰጡ አገልግሎቶች የመለየት፣ የግምገማ፣ ምደባ እና/ወይም አገልግሎቶች አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ አለመግባባትን ለመፍታት አድሎ የሌለበት የችሎት ሂደት ይኖራል።  ችሎቱን ዲስትሪክቱ ወይም ቅሬታ አቅራቢ ገለሰብ ሊያስጀምሩት ይችላሉ።  ቅሬታ አቅራቢ ገለሰቡ ችሎት እንዲያዝለት የሚጠይቀው ከላይ በተጠቀሰው የቅሬታ አቀራረብ ድንብን/ሂደትን በመጠቀም ይሆናል።

ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የማያዳላ የችሎት ባለሙያ (ኦፊሰር) ይሰይማል። የተማሪው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ስለተወሰነው የችሎት መስሚያ ቀን ከ5 የትምህርት ቀናት ቀደም ብሎ በጽሑፍ ይገለጽላቸዋል። የማሳወቂያ ጽሑፉ በወላጁ ወይም በአሳዳጊው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

1. የችሎት መስሚያ ጊዜ እና ቦታ የሚገልጽ፣
2. ወላጁ ወይም አሳዳጊው በጠበቃ/በሕግ አማካሪ የመወከል መብት እንዳለው/ላት የሚገልጽ፣ እና
3. ወላጁ ወይም አሳዳጊው አስፍፈላጊውን ማኅደር የመመርመር መብት እንዳለው/ላት የሚገልጽ፣

ችሎቱ ኢ-መደበኛ እና ተማሪው/ዋ ወይም ወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ የሚገኙበት እና ማስረጃዎችን እና ሌሎች ማረጋገጫዎችን ማቅረብ የሚፈቅድላቸው ይሆናል።  መደበኛ የማስረጃ ደንቦች በዚህ ችሎት የሚተገበሩ አይሆኑም። የተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካዩ በችሎት ቀርቦ ምስክርነት እና ሌሎች ማስረጃዎችን እንዲሰጥ ይደረጋል። ችሎቱ ለሕዝብ ዝግ ይሆናል።

የችሎቱ መኮንን በቀረበለት ማስረጃ ተመሥርቶ ውሳኔውን ለተበዳይ/ለቅሬታ አቅራቢ ግለሰብ እና ለተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ችሎቱ በተጠናቀቀ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት። የችሎቱ መኮንኑ ውሳኔ የማስረጃዎቹን እና የውሳኔ ምክንያቶችን ማጠቃለያ ማካተት ይኖርበታል።

ተበዳይ ግለሰብ ወይም ዲስትሪክቱ ውሳኔው በደረሳቸው በ10 የካላንደር ቀናት ውስጥ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ጥያቄ በማስገባት የችሎት መኮንኑን ውሳኔ እንዲከለስ መጠየቅ ይችላሉ። ጥያቄው በጽሑፍ ሆኖ አቤቱታ አቅራቢው

ያልተስማማባቸውን ውሳኔዎች በዝርዝር መያዝ ይኖርበታል። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የችሎቱን መዝገብ ይገመግማል፣ እንዲሁም ተጨማሪ የጽሑፍ መረጃ ወይም የቃል ምስክርነት ሊጠይቅ ይችላል። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ማመልከቻውን ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ በ15 የትምህርት ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ መስጠት አለባቸው። የዋና ተቆጣጣሪው ወይም የተወካዩ ውሳኔ መጨረሻ ይሆናል።

በዚህ ውስጥ የተካተተ አንዳችም ነገር ለማንኛውም ሰው ከቦርዱ ፖሊሲ፣ ከአስተዳደራዊ ደንቦች፣ ሕጎች፣ ሥርዓቶ፣ ወይም እንዲህ ዓይነት መብት የሚያጎናጽፍ መብት እንደሚሰጥ ተደርጎ የሚተረጎም አይሆንም።

## የውጭ ኤጀንሲዎች

የክፍል 504/ADA ጥሰቶችን በተመለከተ አቤቱታዎች እና የገለልተኛ ችሎት ስሚ ጥያቄዎች በቀጥታ ለOffice for Civil Rights, U.S. Department of Education, 1244 North Speer Blvd., Suite 310, Denver, CO 80204 ሊቀርቡ ይችላሉ።

ሕጋዊ ማጣቀሻ፡-
የ1973ቱ የመልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ክፍል 504፣ 29 U.S.C. § 794
የአካል ጉዳተኞች አሜሪካዊያን አዋጅ፣ 42 U.S.C. § 12101 et seq.
28 C.F.R. § 35.101 et seq.

ማጣቀሻ /Cross Refs./፡-
JB - ከአድሎ የፃ እና እኩል የትምህርት ዕድል